# ዐጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ

ተጻፈ፡
ከነጋድራስ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ባይከዳኝ ።



፲፱፻፲፪ ዓ.ም
አዲስ ፡ አበባ ፡ ኢትዮጵያ ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ዐጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ

ተጻፈ፡

ከነጋድራስ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ባይከዳኝ ።

፲፱፻፲፪ ዓ.ም

አዲስ ፡ አበባ፤ኢትዮጵያ ።

ይድረስ ካቶ ጳውሎስ መናመኖ ወዳጄ ሆይ

እንሆ ከእግዚአብሔር በታች ባንተ ደግነት ከሞት ዳንኹኝ። በብርቱ ታምሜ ተስፋ ቈርጬ በምጥዋ በአስፔዳለ ወድቄ በገንዘብኽ አገዝኸኝ። ለቸሩ ደጃዝማች ገብረሥላሴ በመንገርኽም የበለጠ የደግነት ሥራ አደረግኽልኝ። እንሆም ላገራችን ጥቅም ይኾናል ስል ይህንን ትንሽ ቃል ለመጻፍ በቃኹ። የ ተመሰገነልኝም እንደኾነ ምስጋናው ላንተ ነው። ለኔ ዕድሜ እንዳስጨመርኽልኝ አምላክ ረዥም ዕድሜ ይስጥኽ። ደግነትኽን እስከሞቱ ድረስ ከማይረሳ። ገብረሕይወት ባይከዳኝ።



**ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፡ (፲፰፻፸፱ -- ፲፱፻፲፪ ዓ.ም)**

ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም ትግራይ ውስጥ፣ ዓድዋ አካባቢ ማይ መሻም በተባለ ስፍራ ተወለዱ። አባታቸው ሻለቃ ባይከዳኝ ገብረዝጊ የንጉሰ ነገሥት አፄ ዮሐንስ ፬ኛ ባለሟል ስለነበሩ በንጉሰ ነገሥቱ የመጨረሻ ዘመቻ (የመተማ ዘመቻ) ተሳትፈው በጦርነቱ ላይ ስለሞቱ ሕፃኑ ገብረሕይወት ከእናቱ ጋር መኖር ጀመረ። ከንጉሰ ነገሥት አፄ ዮሐንስ ፬ኛ ሞት በኋላ ትግራይ ውስጥ በሰፈነው አለመረጋጋትና በወቅቱ በአገሪቱ ተከስቶ የነበረው ረሀብ አካባቢውን አስጨንቆት ስለነበር ገብረሕይወት ገና በሰባት ዓመቱ ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ወደ ኤርትራ ተሰደዱ። ኤርትራ ውስጥ ምፅዋ አካባቢ ይገኝ ወደነበረ በአንድ የስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብተው መማር እንደጀመሩ ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ምፅዋ ወደብ ሄዱ። በወቅቱም በወደቡ ላይ መልህቋን ጥላ ወደነበረች መርከብ ውስጥ ገብተው መርከቧን ማየት ይጀምራሉ። የመርከቧ መነሻ ሰዓት ሲደርስ ገብረሕይወት ከጓደኞቹ ተነጥሎ ቀረ። የመርከቧ ካፒቴን የገብረሕይወትን ተደብቆ መቅረት ያወቀው ብዙ ከተጓዙ በኋላ ስለነበር ምንም ማድረግ ሳይችል ቀረ። መርከቧ ከማረፊያ ቦታዋ ስትደርስ ካፒቴኑ ገብረሕይወትን ለአንድ ኦስትሪያዊ ሀብታም ቤተሰብ በጉዲፈቻ እንዲያሳድገው ሰጠው።

ኦስትሪያዊው ቤተሰብም ገብረሕይወትን ተቀብሎት በዚያው መኖር ጀመረ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ትምህርት ቤት ገባ። በትምህርት አቀባበሉ ቀልጣፋና ጎበዝ የነበረው ታዳጊው ገብረሕይወት ብዙ ጊዜ ሳይፈጅበት ጀርመንኛ ቋንቋን አቀላጥፎ መናገር ቻለ። ከዚያም ወደ ጀርመን ሄዶ እንዲማር ስለተወሰነ ወደ በርሊን ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የሕክምና ትምህርት አጥንቶ ተመረቀ። በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት የነበሩት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በመታመማቸው ንጉሰ ነገሥቱ ከጀርመን መንግሥት ሦስት ሃኪሞች እንዲመጡላቸው ጠይቀው ነበር። የጀርመን መንግሥትም ጥያቄውን ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩ ሐኪሞችን ሲመርጥ ሐኪም ገብረሕይወት ባይከዳኝ አንዱ መሆን ቻለ። ይህን እድል በማግኘቱም

አሳዳጊዎቹን አመስግኖ ተሰናበተ። ገብረሕይወት ከሌሎች ሁለት ሐኪሞች ጋር በመሆን ወደ ኢትዮጵያ መጣ።

እነ፡ ገብረሕይወት፡ ኢትዮጵያ፡ ሲደርሱ፡ ንጉሰ፡ ነገሥት፡ ዳግማዊ፡ አፄ፡ ምኒልክ፡ ታመው፡ ስለነበር፡ የተቀበሏቸው፡ እቴጌ፡ ጣይቱ፡ ነበሩ። እቴጌዋም፡ ከገብረ፡ ሕይወት፡ ጋር፡ የመጡትን ጀርመናውያን ሐኪሞች ተቀብለው ገብረሕይወት «ችሎታ አይኖረውም» በሚል ጥርጣሬ የሕክምና ስራ እንዳይሰሩ ከልክለዋቸው ነበር ይባላል። ገብረሕይወት ኢትዮጵያን የለቀቀው ገና የሰባት ዓመት ልጅ ሳለ ስለነበር የኢትዮጵያን ባሕልና ቋንቋ ረስቶት ነበር። ደጃዝማች ይገዙ በሃብቴ ለገብረሕይወት አማርኛ የሚያስተምረው ሰው መደቡለት። በሰባት ወራት ውስጥም አማርኛን በሚገባ አቀላጥፎ መናገር ቻለ። አቀላጥፎ መናገር ብቻም ሳይሆን ከጥሩ ዝርው ስነ-ጽሑፍ ፀሐፊዎች መካከል አንዱ እስከመሆን ያደረሰውን ችሎታ አሳይቶበታል። ከገብረሕይወት መጻሕፍት መረዳት እንደሚቻለው ገብረሕይወት የአማርኛ ቋንቋን እጅግ ተራቅቆ ጽፎበታል።

ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከሕመማቸው ካገገሙ በኋላ ደጃዝማች ይገዙ በሃብቴ እና ነጋድራስ ኃይለጊዮርጊሥ ወልደሚካኤል (በኋላ ቢትወደድ) ለንጉሰ ነገሥቱ ስለገብረሕይወት ነገሯቸው። ንጉሰ ነገሥቱም ስለገብረሕይወት በሰሙት ነገር ተደስተው ገብረሕይወትን አስጠሯቸው። ስለትምህርታቸው ከጠየቋቸውና ካነጋገሯቸው በኋላም የራሳቸው የግል ፀሐፊና አስተርጓሚ አድርገው ሾሟቸው። ገብረሕይወት ገና በሕፃንነታቸው የትውልድ ቀያቸውን ለቀው በመሄዳቸው ከወላጆቻቸው ጋር ተረሳስተው ይኖሩ ነበር። ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክም ይህንን ችግር ተመልክተው አዋጅ አስነግረው ከወላጆቻቸውና ከዘመዶቻቸው ጋር እንዲገናኙ አድርገዋል።

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከሕመማቸው ጨርሰው ሊድኑ ባለመቻላቸው ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፩ ዓ.ም ልጅ ኢያሱ ሚካኤል የዙፋናቸው ወራሽ

መሆኑን በአዋጅ አሳወቁ። ይህንን ሐሳባቸውን ለውጭ መንግሥታት ለማሳወቅ በፈለጉ ጊዜም ወደ ውጭ መንግሥታት በተላከውና በደጃዝማች መሸሻ ወርቄ በተመራው የልዑክ ቡድን ውስጥ ገብረሕይወት አባል ነበር። የልዑክ ቡድኑም የተላከበትን ተግባር አከናውኖ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል።

# ፮

ታሪክን መማር ለኹሉ ሰው ይበጃል ለቤተመንግሥት መኰንን ግን የግድ ያስፈልጋል የዱሮ ሰዎች ስሕተትንና በጐነትን አይቶ ለመንግሥቱና ላገሩ የሚበጀውን ነገር ያውቅ ዘንድ። የታሪክ ትምርት ግን የሚጠቅም የውነተኛ ታሪክ ትምርት ሲኾን ነው። እውነተኛንም ታሪክ ለመጻፍ ቀላል ነገር አይዶለም የሚከተሉት ሦስት የእግዚአብሔር ስጦታዎች ያስፈልጋሉና። መዠመሪያ ተመልካች ልቦና-የተደረገውን ለማስተዋል ኹለተኛ የማያዳላ አእምሮ-በተደረገው ለመፍረድ ሦስተኛ የጠራ የቋንቋ አገባብ-የተመ ለከቱትንና የፈረዱትን ለማስታወቅ። ያገራችን የታሪክ ጻፎች ግን በነዚኽ ነገሮች ላይ ኀጢአት ይሠራሉ። በትልቁ ነገር ፈንታ ትንሹን ይመለከታሉ ለእውነት መፍረድንም ትተው በአድልዎ ልባቸውን ያጠባሉ አጻጻፋቸውም ድብልቅልቅ እየኾነ ላንባቢው አይገባ ም። ይህም ነገር በቤተመንግሥትና በየገዳሙ ከሚገ ኙት ታሪከ-ነገሥታት ጥቂት ብራኖች ብናነብ ወዲ ያው ይገለጽልናል የታሪካችንም ጻፎች ኹለት ዐይነ ት ሰዎች እንደኾኑ እንረዳለን። አንዱ ዐይነት የቤ ተመንግሥት ሊቃውንት ይባላሉ ማለት እንጀራን ሲፈልጉ ከቤተመንግሥት ተጠግተው ንጉሡ ያዘዛቸ ውን የራሱን ውዳሴ ታሪክ ብለው ጽፈው ለኋላው ትውልድ የሚያስቆዩ አቈላማጮች። ኹለተኛው ዐይነት ግን መነኮሳት ናቸው-እነሱም የሚጽፉት ታሪክ አድልዎ ይበዛበታል የራሳቸውን እንጂ የሕዝቡን ጥቅምና ጉዳት ከቶ አያቋጥሩምና ስለዚህ የልባቸውን የሚፈጽምላቸውን ንጉሥ ቅዱስ ቅዱስ ይሉታል ከድንቍርናቸው ወጥቶ ከፍ ባለ ኀሊና ተመርቶ ስለዜጎቹ ልማት የሚጥር ግን ርኩስ። አውራ ጐዳናንና ድልድዮችን ከሚያስበጅ የጥበብንም ማስተማሪያ ቤቶች ከሚከፍት ንጉሥ ይልቅ የመንግሥቱን ጉዳይ ኹሉ ረስቶ ከናዝራዊ ከሌላም ዐይነት መኖከሴ የሚውል ሥራ ፈትተው ለሚኖሩቱ መኖኮሳትም ምግብ ብሎ ብዙዎች

አገሮች የሚጐልት ንጉሥ በነሱ ዘንድ ይመሰገናል። ያገራችንም የታሪክ ጻፎች ውዳሴ ከንቱና ስድብ እውነተኛውን ታሪክ አይተው የማይመስለውን ተረት የሚወድ ባይኾን ምንም ባልጎዳነም ነበር። መጽሐፋቸውንም አንቦ እውነቱን መርምሮ ለማግኘት አእምሮ ላለው ሰው ባላስቸገረው ም ነበር። እጅግ ያሳዝናል እስካኹን ድረስ ያበሾች ታሪክ በጨለማ ተሸፍንዋልና። አባቶቻችን ከባሕር ማዶ ተሻግረው መጥተው ይህነን አገር ሲያቀኑ ያገኙትን ድካም ከድካ ሙም በኋላ አኵስማውያን ተብለው የደረሱበትን የ ክብረት ከፍታ ቀጥለውም በሃይማኖት ልባቸው ተለያይቶ መዠመሪያ አረመኖችና ፈላሾች ኹለተኛም ፈላሾችና ክርስቲያኖች ቆይተውም ክርስቲያኖችና እስ ላሞች እየተባባሉ እርስ በርሳቸው ተፋጅተው ዝቅ ብሎ ጠፍቶ የነበረው መንግሥታችን ባባታጠቅ ቴዎድሮስ ሲታደስ በወሬሳው ካሣም ሲዋሃድ እንዴት እንደነበረ ባባዳኘው ምኒልክም እንዴት አርጐ ሰፍቶ እንደረጋ ገልጾ የሚያወጋን የታሪክ ጸሓፊ መች ይወጣ ይኾን። ይህ ምኞት እስከብዙ ጊዜ ድረስ የሚፈጸም አይመስልም። አኹን በዘመናችን በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ የኾነውን ነገር እንኳ አጥ ርተን ለማወቅ ያልተቻለን የዱሮውን እንሻን እስከ ዛሬ ድረስ እኮ ልከኛ ያጤ ምኒልክ ታሪክ አልተ ጻፈም። ነገሥታት በሕይወታቸው ሳሉ ታሪካቸውን ያለፍራት የሚጫወቱበት ያርነት ጊዜያት ላበሻችን ገና አልወጣም። ደግሞም እንደአገራችን ሰው ትምር ት የሌለው ሕዝብ እውነቱን ሊሰማ አይወድም ቢ ሰማም አይገባውም። አንድ ንጉሥ እንዴህ አርጎ ጥሮ ነገሠ ከነገሠም በኋላ በእንዴህ ያለ ምክንያ ት ይህንን ፈጸመ ይህንንም ተወ በንዴህ ያለም ነገር ወደቀ ወይም ለማ ከሚልዋቸው ይልቅ እገሌ ከሰማይ ወይም ከጠንቋይ እንደዚህ ያለትንቢት መጥቶለት ለመንግሥት የተወለደ ሰው መኾኑን ዐውቆ ታውቆ እገሌና እገሌ ታጠቁለት እገሌና እገሌም ሰይጣን አስቶዋቸው ተዋግተውት አሸነፋቸ ው ነገሠም ከነገሠም በኋላ እገሌ ቅዱስ ወይም ናዝራዊ መክሮት ይህንን አደረገ ከሰይጣንም ቢፋቀር እንዴህ ያለ ጉዳት ወረደበት በፍካሬየሱስ የተተነባውም ጊዚያቱ ተፈጽሞ ሞተ ብለው ቢዋሹላቸው ይወዳሉ።

ጉልበት የሌለው ብዙ ንጉሥ ኑረዋል ይኖርም ይኾናል ነገርግን የታሪካችን ቃል እውነት ከኾነ ዘንድ እንዴሁ በብዙ የቅዱሳንና ያጋንንትን ርዳታ እንደ ኢትዮጵያችን ነገሥታትና ገዥች የሚያስፈልገው ሰው በዓለሙ ታሪክ ከቶ አልተሰማም።

ከዚህ ቀደም የሚወጋውና የተጻፈው ያጤ ምኒልክ ታሪክም ትክክል አይመስልም። አቶ ገብረየ ሱስ አፈወርቅ ከጻፉትም መጽሐፍ በቀር ፍሬ የሚ ገኝበት ነገር ለሸዋው ነጉሥ ገና አልተጻፈላቸውም። ያ ካቶ አፈወርቅ እጅ የታተመ ታሪክም ቢኾን ምሉ አይዶለም። ብዙውን ነገር በጨለማነቱ ይተዋል ብዙውንም ነገር ያሳምራል በየዋሁ በጠንካራውም የትግሬ ነገድ ይልቁንም በንደ ወሬሳ ካሣ ያለአርበኛ ከማንም ሰው እንጅ እንደአቶ አፈወርቅ በሊቅነቱ ከተጠራ ሰው እጅና አፍ ሊወጣ የማይገባው የስድብ ቃል ይገኝበታል። ዳግማዊ ምኒልክንም ለማመስገን ዳግማዊ ዮሐንስን መስደብ የሚያስፈልግ ያስመስላል። ስለኾነ የትምርት ወዳጅ የኾነ በመልካም ዐማርኛም የተጻፈ መጽሐፍንም ማንበብ የሚወድ ኢትዮጵያዊ ኹሉ ያንን መጽሐፍ ያደረገ አድርጎ ገዝቶ ሊያየው ይገባል።

እነዚህን ጥቂቶች ቃሎች የሚጽፍ ሰውም ቢኾን ያጤ ምኒልክን ታሪክ ዐውቃለኹ ብሎ አይ መካም ሊጽፍም አይከጅልም። ከዚህ ቀደም ከተጻፉ ቱ ውሸቶች ላይ ሌላ ውሸት ሊጨምር አንዳች ፈቃድ የለውምና። አሳቡስ ድፍረት ኾኖ እንዳይቆጠ ርበት ይፈራል እንጂ ዳግማዊ ምኒልክ ስለሕዝባቸው ልማትና ትልቅነት ምን እንደጣሩ ምንስ ሳይጥሩ እንደቀሩ ለማመልከት ነው።

# ፪

ዐጤ ምኒልክ በ፲፫ ነሐሴ ፲፰፻፴፮ ዓ.ም ባበሻ ቍ ጥር ባንኮበር ከተማ ከሸዋው ንጉሥ ኀይለመለኮትና ከወይዘሮ እጅግአየኹ ተወለዱ። ካጤ ተክለጊዮርጊስ ፍጻሜ መንግሥት ዠምሮ አጤ ምኒልክ ተወልደው ያሥራኹለት ዓመት ልጅ እስኪኾኑ ድረስ አገራቸው ሸዋ ባላባቶቹን እያሠለጠነ ከቀሩቱ የኢ ትዮጵያ አውራጆች ተለይቶ ለብቻው መንግሥት አቁሞ ነበረ።

በ፲፰፻፵፯ ዓ.ም ግን ንጉሥ ኀይለመለኮት ሙተው ትልቅ ጦርነት ሳይኾን ዐጤ ቴዎድሮስ አ ገሩን ወደመንግሥታቸው ጨመሩት። አጤ ምኒልክም ከብዙዎች የሸዋ መኳንንት ጋር ተማርከው ወደበጌ ምድር መጡ። የኻያ ዓመት ጐበዝ ኹነው ከድተው ወዳገራቸው እስኪመለሱ ድረስም ባጤ ቴዎድሮስ ቤተመንግሥት በክብረት አደጉ። ዐጤ ቴዎድሮስ ከሞቱም በኋላ መንግሥት ሊይዙ ጣሩ እንደማይኾንላቸው አይተው ግን ላጤ ዮሐንስ ታጠቁ። ዐጤ ዮሐንስም በመጋቢት ፲፰፻፹ ዓ.ም በመተማ ጦርነት ከሞቱ በኋላ የሸዋው ባላባት ወደረኛ የሚኾን ሰው አልተገኘም። በዚህ ምክንያት በ፳፯ መስከረም ፲፰፻፹፪ ዓ.ም ዐጤ ምኒልክ የንጉሠነገሥትን ዘውድ በንጦጦ በእመቤታችን ቤተክርስቲያን ጫኑ።

ከነገሡ እስከዛሬ ያለፈውም ዘመን ብንመለከት እጅግ የታደሉ ንጉሥ እንደኾኑ ይገልጽልናል። የድላቸውም ኮከብ እስኪታመሙ ድረስ አልተለያቸውም። እንደነ ዐጤ ቴዎድሮስ እንደነ ዐጤ ዮሐንስም ዕድሜያቸውን በድንኳን አላሳለፉትም። ነገር ግን አንድ ጊዜ በንጦጦ አንድ ጊዜ ባዲስዓለም አንድ ጊዜ ባዲስ አበባ በደመቀ ቤተመንግሥት አርፈው በሰላም ተቀመጡ። ህውከተኛውም ያበሻ ሕዝብ ሰላማዊ ኾነላቸው። አንባቢው በምን ምክንያት ብሎ ይጠይቅ ይኾናል ዐዲስ የሚበጅ ሕግጋት ስላወጡ ወይስ ለሕዝቡ (ላቶ አፈወርቅ እንደሚመስላቸው) ትምርት

ስለገለጹለት ይኾንን? የሸዋ ሰው አዎን ይላል። ትግሬውም ባላባቶች እርስበእርስ እየተመቃኙ አስገዝዋቸው ብሎ ያወጋል። ስሜን በጌምድር ላስታ የጁ ግን እቴጌ ጸሓይቱን በማግባታቸው እኛን ያኽል ኀይለኛ ረዳት ስላገኙ ነው ብሎ ይመካል። ባጤ ዮሐንስ ጠፍቶ የነበረው ጐጃም በቸርነታቸው ያመካኛል ጋላውም ኹሉን ከሚችል ብርታታቸው የተነሣ ነው ይላል።

እስኪ የማናቸው ነገድ አሳብ እውነት እንደኾነ እንመርምር። ጥቂትም ብናስተውል ከትግሮቹና ከሸዎቹ በቀር ኹሉም እውነታቸውን እንደኾነ ይገባናል። ይልቁንም ጋላ የዳግማዊ ምኒልክን ኀይል ሊፈራ ሥርዐት ነው። ኢትዮጵያ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ከግራኝ ወዲህ አይታው የማታውቀውን ብርታት ስፋትም አግኝታለች። ዛሬ መንግሥታችን እንኳን ባገራችን ውስጥ በውጭ ነገሥታትም ቢኾን ኀይሉ ታውቆለታል። ነገር ግን የጤና መሠረት የሌለው ቤት ቢይዙ ዕድሜ ያገኛል ተብሎ እንደማይታመን እንዲሁም መንግሥታችን መሠረት ያለው ሥርዐት እስኪያገኝ ድረስ ኀይሉ ብዙ ዓመታት ይቆያል ተብሎ አይታመንለትም። ይህ ነገር እውነት መኾኑን የሚጠረጥር ሰው ቢኖር ለሚከተለው ነገር ጆሮ ቢሰጥ ይረዳዋል።

ከሦስት ዓመት በፊት ንጉሡ ታመው ያገራችን መኳንንት ኹሉ ወደ ዐዲስ አበባ ተጠሩ። ያገራችን መኳንንት ወደ ጌታቸው ሲጠሩ ዐሥር ወይም ኻያ ራሳቸው መኼድ ነውራቸው ነው። ስለዚህ ያንን የተሾሙበትን አገር ለመጠበቅ የሚበቃ ሠራዊት ሳይተው ወደጦርነት የታዘዙ ይመስል አስከትተው ይጓዛሉ። ጉዞዋቸው የኢጣልያ ሰው እንዳለው የጦር መልክ የለውም ነገር ግን ወደስደት የተነሣ ሕዝብ ይመስላል። ከዛሬ ሦስት ዓመት በፊትም እንዴሁ ያገራችን ጌቶች ወደንጉሡ ከተማ በተጠሩ ጊዜ በዳርአገር ሲኖር የነበረው ያማራ ዘር ኹሉ ጨቅላን ያዘለች ሴት ሳትቀር ወደ ዐዲስ አበባ ተጓዙ። ጋላውም ይህንን ቢያይ ተገረመ ንጉሡ ሞቱ ብሎም አወራ በየሥፍራውም ሊሸፍት ከጀለ በእግዚአብሔር ቸርነት ሳይኾንለት ቀረ እንጂ።

እንሆ እንኳን አእምሮ ያላቸው ነገሥታት ኃላውም ቢኾን የመንግሥታችን ችሎት ነዋሪ ነው አይልም። ንጉሡ ቢሞቱ መንግሥታችን የሚሞት ይ መስለዋል። እውነትም ነው። ትምርት በሌለው ዘንድ ንጉሥ ማለትና መንግሥት ማለት ትርጉሙ አንድ ነው። ንጉሣቸውም የፈቀደውን ያደርጋል በመላው ሕዝቡ ባሮቹ ናቸው። ጌታቸው እንደሞተባቸው ባሮ ችም ንጉሥ በሞተ ቁጥር እኔ ልበልጥ እኔ ልበል ጥ ሲሉ ይጣላሉ ቶሎ ብሎም አንድ የሚገተይባ ቸው ሰው ያልወጣ እንደኾነ እርስ በርሳቸው ይፋ ጃሉ። ደግሞም ባሪያ ለጌታው ልጅ በግድ ካልኾነ በቀር ወዶ እንደማይገዛ እንዲሁም አእምሮ የሌለ ው ሕዝብ የንጉሡን ልጅ ብሎ አያቅፍም። አእም ሮ ባላቸው ሕዝቦች ዘንድ ግን መንግሥት ማለት ማኀበር ማለት ነው። ንጉሣቸውም የማኀበራቸው አ ለቃ ማለት ነው። ስለዚህ ንጉሡ የፈቀደውን ያደር ግ ዘንድ አይችልም ሥልጣኑ የሕዝቡ ማኀበር በ ደነገገው ሕግና ወግ የተወሰነ ነው። የማኀበር አለ ቃ ሲሞት ማኀበር እንደማይፈርስ እንዴሁ ንጉሣቸ ው ቢሞት አእምሮ ያላቸው ሕዝቦች ግድ የላቸ ውም። ንጉሥ ቢሞት ያ በሥራት የሚገባው ወራሽ ይተካል። ንጉሥ ሙተዋል ዕድሜ ለንጉሥ ነው ከ ነምሳሌው። በጐንደር ዐጤዮችም ቢኾን ንጉሥ በሞ ተና በነገሠ ቁጥር እንዴህ ሲታወጅ ነበር ‘የሞት ንም እኛ ያለነም እኛ በያለኸበት ርጋ።

አእምሮ የሌለው ሕዝብ ሥራት የለውም። ሥራትም የሌለው ሕዝብ የደለደለ ኀይል የለውም። የ ኀይል ምንጭ ሥራት ነው እንጂ የሠራዊት ብዛት አይዶለም። ሥራት ከሌለው ሰፊ መንግሥት ይልቅ በሕግ የምትኖር ትንሽ ከተማ ሞያ ትሠራለች ስለ ዚህ ኃላው ዐጤ ምኒልክን ቢፈራ መንግሥታችንን ግን ቢንቅ እውነቱ ነው። መንግሥታችን ይህንን ዓ መት ምሉ የታፈረች በምኒልክ ግምባር ነው እንጂ በሥርዓታችን ደልዳላነት አይዶለምና።

እንግዴህ ይህንን ካወቅነ ዘንድ የትግሮችን ወግ እንመርምር። ትግሬ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ፈጽሞ ጠፍተዋል። የትም የትም ብትኼድ በዚያች

አገር የለማ መንደር አታገኝም። ሰው ከሚኖርባቸው ም ጐጆችዋ ይልቅ የድሮ ልማትዋን የሚመሰክሩ ፍራሾችዋ ይበዛሉ። የትግሬም ጐበዝ በዛሬ ዘመን ባባቱ አገር አይገኝም አውራ እንደሌለው ንብ ድ ርሻው ሳይታወቅ ወደአራቱ የዓለም መዓዝኖች ተዘ ርትዋል እንጂ። ባገሩም ላይ ድኽነት ሰፍታለች የ ሌሎች ወገኖች መተረብያ እስከትኾን ድረስ። ኹሉ ም መሬት በሰላም ሲኖር ምስኪኒቱ ትግሬ ግን ሽፍታና ወንበዴ አልተለያትም። ባላባቶቹም ዘወትር እርስ በርሳቸው ሲዋጉ ይኖራሉ። ምስኪኑም የትግሬ ባላገር ዐጤ ምኒልክ ያጣልዋቸው እየመሰለው በሸ ዋው ንጉሥ ላይ ብዙ ይፈርዳል። ዐጤ ምኒልክን የ ሚያውቅ ሰው ግን ይህንን ሐሜት ሲሰማ ይሥቃል። የቸሩ ምኒልክን ባሕሪ የያዘ ሰው ያፋቅራል እንጂ አያጣላም። ሰውንም ፈጽሞ ሊጐዳ አይችልም። የማያ ውቃቸው ሰው ግን በብዙ ክፉ ነገር ያማቸዋል። አኹን ድንገት አንድ መኰንን ታሞ በሽዋ መሬት ቢሞት እግዚአብሔር ገደለው አይባልም ነገር ግን ያጤ ምኒልክ መድኀኒት። የደንቆሮ ሕዝብ ንጉሥ መኾኑን ያንድ ወገን ጥቅሙ ብዙ ሳለ ሐሜት ያመጣል። ሌላስ ይቅርና ሰማይ ዝናብን ባይሰጥ እ ርሻም ብዙ አላፈራም ቢል ትምርት የሌለው ሕዝ ብ በንጉሡ ያመኻኛል። እንዴሁም ትግሬ ባጤ ም ኒልክ ተጐዳ ቢባል ሐሰት ነው እርስ በርሱ መስ ማማት ስላጣ ተበላሸ እንጂ። ትግሬን የሚያኽል ትልቅ ያርበኞች ነገድ እርስ በርሱ ከተስማማ ዘን ድ ሊጐዱት አይቻልም። ዐጤ ምኒልክ ግን ባንዲት ነገር ሊታሙ የተገባ ነው። የትግሬን ሕዝብ እንደ ሕዝባቸው አልቈጠሩትም። በትግሬ መሬት ሽፍቶ ባላገሮችን ሲያጠፋ የነበረው ወንበዴ ኹሉ ሲገባላ ቸው ምረው ሲሾሙት ሲሸልሙት ነበሩ። ይህም በደል በወራሻቸው እንዳይደገም ተስፋ እናደርጋለን። እውነትም በትግሬ ነገድ ልማትና ጉዳት ምን ቸገረ ኝ የሚል ንጉሥ ለራሱ ይጐዳል። ትግሬን የሚያኽል ትልቅ ነገድ ቢጠፋ ለኢትዮጵያ ታላቅ ጉዳት ነው ቢለማና ቢመቸው ግን ታላቅ ጥቅም። የኢትዮጵያ መሠረት ትግሬ ነው። ከቀሩቱም የኢትዮጵያ ነገዶ ች ይልቅ የኢትዮጵያን መንግሥት ዕድሜ ሊመኝ የሚገባው ትግሬ ነው። ይህ ግን ከብልኀ ደጃች ገብረሥላሴ በቀር በሌሎች የትግሬ መኳንንት ዘን ድ

አልታወቀም። እኒያ ጠንካራ የኀይሌ ልጅ ግን እንደነተድላ ዋህድ እንደነአሉላ አባነጋ ዱሮ ዘመን በጐራዴያቸው እንዳደረጉ እርሳቸውም ደግሞ ዐዲስ አበባ ላይ ኹነው በምክራቸው የትግሬ ሰው የኢት ዮጵያን መንግሥት ዕድሜ እንዲመኝ መሰከሩ። የሚበዛውም የትግሬ ሰው እንደርሳቸው ያስባል።

እንግዴህ ከጸሓፊው ልብ ውስጥ ፍርሃት ተነሣ የሸዎቹን አሳብ ሊመረምር ነውና። ዘመናይ ኹሉ ሊያመሰግኑት እንጂ ሊወቅሱት አይወድም። ስ ለዚህ ብዙ የሸዋ ሰው ሳይቆጣ አይቀርም። ነገር ግን ሰውን ፈርቶ እውነቱን የሚሸሽግ ሰው እንደ ወንድ ይቆጠራልን መንግሥቱንም የሚወድ ሰው ያ ቅዱስ ቅዱስ የሚለው አይዶለም ጥፋቱን ይገል ጽለታል እንጂ።

እንግዴህ ወደ ምርምራችን እንመለስ። ዐጤ ምኒልክ በእውነት የሸዋ ሰውና አቶ አፈወርቅ እን ደሚሉት ዐዲስ ሕግጋት አውጥተዋልን? ትምርትንስ ገልጸዋልን?እውነት አይዶለም። ይህማ ቢኾን ይኸን ያክል ጊዜ እንጀራቸውን በሰላም አይበሉም ነበር። ትግሬው አለቃ ተወልደመድኅን እንደሚሉት ‘መብ ራት ሳይነድ አያበራም። ስለዚህ የዓለምን ታሪክ ብንመለከት ዐዲስ ሥርዐት የሚያወጣ ንጉሥ ኹሉ በሕይወቱ ሳለ መከራ አይለየውም ሕዝቡ እንደአ ውራ ደመኛው ያየዋልና። ደግነቱም የሚታወቅ ብዙ ዓመታት ከሞተ በኋላ ነው። የአዳምን ዘር ባሕሪ በጠቅላላው ብንመለከት ዐዲስን ነገር የሚወድ ወ ገን አናገኝም። ካባቶቹ የቆየውን ካልኾነ በቀር ይ ልቁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያባቶቹን ልማድ ሲለ ውጡበት ዝም ብሎ ባልተቀበለም ጢስ እንደገባበ ት ንብ በተሸበረ በተናወጠም ነበር እንጂ። ወዮለት! ለዚያው ንጉሥ የዛሬውን ከደማችን ጋራ የተዋ ሀደውን የድንቁርና ሥርዐታችንን ሊለውጥ ለሚነሣ ው!ለኋላ ስም ያገኛል እንጂ በሥጋው አይጠቀምም።

ይህም ነገር ባጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ይመሰ ክርናል። ያ ቋረኛ ንጉሥ ተበጣጥሰው የነበሩትን ያ በሻን መንግሥት ክፍሎች በሰላው ጐራዴው ቀጥ ቅጦ አዋደደ። ሕዝቡንም ከካህናትና ከሹሞች ቀምበ ር አርነት ሊያወጣ አገር በጁ ብሎ ዐወጀ ትም ርትንም ሊከፍት ተከራከረ። አንባቢ ሆይ! በዚህ ጥረ ቱ ምን ተጠቀመ ይመስልኻል በመላው ሕዝብ በካህናትና በሹሞች ተመክሮ ተነሣበት አሳበደውም። በመጨረሻም ለባዕድ አሳልፎ ሰጠው በገዛ እጁም ሞተ። አእምሮ የሌለው ሕዝብና ልጅ ጠቃሚውን አይወድም። የቴዎድሮስ አሳብ ግን አልተፈጸምም እ ንጂ አልሞተም። አባታጠቅ ለራሱ ቢከፋው የማይረሳ ውን ስም ተክሎ ሞተ። እውነት ነው የመነኮሳት ኀ ይል ገና አላላችም ሹሞቹም ብርቱ ተቋጣጣሪ ገ ና አልወጣላቸውም። እስካሁንም ድረስ የተሾሙበትን አገር በገንዘባቸው እንደገዙት ርስት ያዩታል። ከሱ በሚወጣውም ግብር የታያቸውን ያደርጋሉ በታቻቸ ውም ያለ ሹምና አሽከር ከነሱ በቀር ሌላ ጌታ አያውቅም አጣም አገኘም ከቸርነታቸው ነውና። የ ኾኖ ኾኖ የዛሬ ሹማምንት እንደዱሮቹ አይዶሉም መንግሥት በላያቸው እንዳለ ጥቂት ይታወቃቸው ጀምረዋልና። እያደረም አጥብቆ ሳይታወቃቸው አይ ቀርም። ስለዚህ የቴዎድሮስ መንፈስ አልሞተም እያ ደረ ሕይወት ይጨምራል እንጂ።

የሽዋው ንጉሥ ግን ለሕዝባቸው ያባቱን ልማድ መረቁለት ዐዲስ ነገር እንዲቀበልላቸውም አልተከራከሩትም። ወንበዴውም ኹሉ እንዲያርፍላቸው ስለሥርዐት የሚበቀል ጐራዴ አልመዘዙበትም ነገር ግን በቸርነታዊ እጃቸው ወዳደባባያቸው ስበው ደ ጅ አስጠኑት ሹሞቻቸው ግብር ብለው ከሚያመ ጡላቸው ጥቂት ሲሳይም መገቡት። በራሱ ላይ ቆቡን ጭኖ ወይም ትልቁን ሻሽ ጠምጥሞ ወይም መቋጠሪያ ይዞ ወደ ዐዲስ አበባ ቤተመንግሥት ሊለምን የኼደም ሰው ኹሉ ባዶ እጁን አይመለስም ነበረ። ስለዚህም ትልቁም ትንሹም 'ቸሩ ምኒልክ' ይል ገባ ይላልም። ስለዚህም ጐዣሞች እንደሚሉት ዐጤ ምኒልክ በቸርነታቸው

ገዙ ቢባል ውሸት አይዶለም። ይህ ማለፊያ ነው ያስመሰግናልም ግን ትምርት ገለጹ አያሰኝም።

አንድ ልበ-ብሩህ ያበሻ ሰው መሬት ትዞራለች ብሎ ቢያስተምር አኹን በቅርቡ በሐረርጌ በዳኛ ተይዞ አልነበረምን? አኹን ፲፱፻ ዓመታት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ዐልፈው ኻያኛውን መቶ ዓመታት ስንዠምር አንድ ሰው የተዋህዶን ሃይማኖት ቢነቅፍ ካዲስ አበባ ገበያ ላይ በደንጊያ አልተቀጠቀጠምን? እስከዛሬ ድረስሳ ወደሩቅ አገር ተሰደው ወይም ወደአበሻችን ከሚመጡት ፈረንጆች ጥቂት ጥበብ ተምረው ያገራቸውን መንግሥት ሊጠቅሙ የሚፈልጉ ወንድሞቻችን ጵሮተስታንት ካቶሊክም መናፍቃን የሌላ መንግሥትም ሰላዮች እየተባሉ ሲራቡ ሲከሰሱም እናይ የለምን? የነዚያን መከረኞች ስም ስንት ብለን እንቍጠር? የሚከተሉቱ የኹለት ሰዎች ስም ግን እንዲወሱ የግድ ነው እነሱም ከን ቲባ ገብሩና አለቃ ታየ ናቸው። ሦስት ዓመት ሙሉ ዐዲስ አበባ ላይ ስቀመጥ እንደነዚህ ኹለት ሰዎ ች አርጎ መንግሥቱን የሚወድ ሰው አላየኹም። ይህ ደግነታቸው ግን እስከዛሬ ድረስ አልታወቀላቸውም ይመስለኛል። እጅግ ያሳዝናል የነሱን ዕድል ያየ ሰው የኢትዮጵያ መንግሥት ለወዳጁ አይጠቅ ምም ብሎ ተስፋ ይቆርጣልና።

ጃፓን የሚሉት መንግሥትስ እንኳን ተምሮ የመጣለትን ሊያበርር ወደኤሮጳ ኺዶ የሚማርለትን ሲያገኝ በገንዘብ ያግዘው ነበር። የትምርትን ቤት እከፍታለኹ ብሎ የሚመጣውንም የኤሮጳን ሰው እንኳን ሊከለክል በገንዘቡ እንዲመጣለት ይዋዋለው ነበር። ስለዚህም ሕዝቡ ዐይኑን ከፈተ ሀብታምም ኾነ በረታም ታፈረም። ቺናና አስያም የሚባሉ ኹ ለት መንግሥታትም የጃፓንን መንገድ በብዙ ትጋት መከተል ዠምረዋል።

ዐጤ ምኒልክም እንደርሱ ያለውን መንገድ መከተል ይገባቸው ነበር አልተከተሉትም እንጂ። የ ሸዋ ሰው ሆይ! እንግዲህ ዐጤ ምኒልክ የገለጹት ትምርት የት አለ ለራሳቸው አስተማሪ የሚፈልጉ ግብጦች

ከሚያስተምሩባቸው ኹለት የትምርት ቤቶ ች በቀርሳ የሚረባውን ሌላ የትምርት ቤት እስቲ አሳየኝ የታወጀውን ዐዲስ የመሠረተ ሥርዐት እስ ቲ አሰማኝ የሸዋ ሰው ሆይ! ስለምን ዝም ትላለኽ ወዲያው ተረታኽን ዐጤ ምኒልክ ሕዝባቸው እንዲ ማርላቸው ይመኙ ነበር ብትል ግን እውነትኽ ነ ው። ለራሴ ይመቸኝ እንጂ በኋላዬ በሚኾነው ነገ ር ምን ቸገረኝ ይሉ ያስቡም እንዳልነበሩም አስተ ዋይ ኹሉ ያምንላቸዋል። ስለሕዝባቸው ደኅንነትና ብርታት የሚበጀውን ብዙ ነገር ሲያስቡም እንደነበ ሩም ውልውል የለውም። ይልቁንም ሊታመሙ አቅ ራቢያ ብዙ ትልልቅ ነገር ዠመሩ ሊፈጽሙትም ቈርጠው ነበር ነገር ግን ኹሉም በውጥን ቀረ። ምስኪን ኢትዮጵያ ሆይ! የዕድልሽ ቀን መች ይነጋ ይኾን? ዐጤ ምኒልክ ይህን ያኽል ጊዜ በጤና ሲኖ ሩ ኑረው በብርታት ሊጥሩልሽ ሲነሡ በበሽታ ተያ ዙ። ይህም ያጤ ምኒልክ ነገር እጅግ ይገርማል ኽያ ዓመት ምሉ ዝም ማለታቸው በሽታ ወይም ሞት ይመጣብኛል አይሉም ኑረው ይኾን? ምኒልክን የሚያኽል ሰው በንዴህ ያለ ድንቁርና አይታማም። እውነቱስ ይህ ነው-ዐጤ ምኒልክ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የኤሮጳ ነገር ፈጽሞ ሳይገለጽላቸው ቀርቶ ነበረ። ሕዝባቸውም የኤሮጳን አእምሮ ያላቀፈ እንደ ኾነ ጠፊ መኾኑን አልተረዱትም ነበር። በዚህም ነ ገር ሊነቀፉ አይገባም። ማን ቢያስተምራቸው ማንስ ይህንን ነገር ቢገልጽላቸው ሳይገባቸው ቀረን ባንድ ወገን ትምርትን የማይወድ ሕዝብ አጠራቸው ባን ድ ወገንም ሲያምኑዋቸው በነበሩ ፈረንጆች ብዙ ተታለሉ። ስለዚህ አማካሪ የሚኾናቸውን የኤሮጳን ሰ ው እንዳያስመጡ ሠጉ። ኋላ ኋላ ግን ወደግዛታቸ ው የሚመጡቱ ፈረንጆች ቢበዙ ጨዋውንና ክፉው ን ለዩ። ሹማምንቶቻቸውም ይልቁንም ነጋድራስ ኀ ይለጊዮርጊስና ነጋድራስ ይገዙ የባሕር ማዶን ሥርዐ ት በትጋት እየጠያየቁ ጌታቸውን መንግሥትን በሚ ጠቅም ምክር ያግዙ ዠመሩ። ንጉሡም በጊዜ ብዛ ት ነገሩ ገባቸው። ብሩሁ ልቦናቸውም ብዙውን ት ልልቅ ነገር ሊፈጽም በብዙ ብርታት ተነሣ ዠመ ረም የድንገት በሽታ ግን ብርታቱን አደከመበት። መድከማቸውንም አይቶ ደኻው በየጐጀው አለቀሰ ያ ለቅሳልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

በንዲያው እንኳ ይህን ያኽል ያለቀስኽ ምኒልክ አስቦልኽ የነበረው ልማት ተገልጾልኽ ቢኾን ምን ትል ኑርኻልን?

ደግሞም አንድ ነገር እንጠይቅ። ንጉሡ ቢ ታመሙ አሳባቸው ስለምን በውጥን ቀረ? የሚፈጽመው ሰው ታጣን? አዎን። የሚበዙቱ ሹማምንቶቻቸው እንኳን የታሰበውን ነገር ሊፈጽሙ የተፈጸመውም ቢፈርስ ግድ የላቸውም። የሹሞቹም ስንፍና አያስደን ቅም ካለመማራቸው የተነሣ ነውና። ያልተማረ ሰው ኹሉ የራሱን እንጂ ያገሩንና የመንግሥቱን ጥቅም ሊያስብ አይችልም። ስለዚህም በገንዘብ ይታለላል ቢኮረፍም ይሸፍታል ስለመንግሥቱም ልማት መከራ ን ችሎ ተዋርዶ ከሚኖር ብዙ ሰውን ፈጅቶ አገ ርንም አጥፍቶ ቢሞት ወይም ቢታሰር ስም ይመስ ለዋል። ስለዚህ የሹሞቹ ቸልታ ፈጽሞ ይገባል።

ፈጽሞ የማይገባስ የእቴጌ ጣይቱ ነገር ነ ው። እኒያ ክብርት ሴት አገራቸውንና ሕዝባቸውን ሲወዱ እንደነበሩ ማን ይጠረጥራል? ለኢትዮጵያም መንግሥት ብዙ እንዳገለገሉ ማን አሌ ይላል ባ ጤ ምኒልክ ጊዜ አገራችን የረጋች ስሜነኞችና በጌምድሮች እንደሚሉት በጣይቱ ብጡል ብርታት ነው። እውነታቸውም ነው ምክንያቱ እነሱ ከሚፈክሩ ት ሌላ ኾነ እንጂ። እቴጌ ጣይቱ የሸዋን ቤተመ ንግሥት እልፍኝ ባይዙ የሸዋ ወንድሞቻችን እናጠ ቃለን ሲሉ ባገራችን ላይ ሰላም አይሰፍንም ነበር። በሸዎች አሳብ ከድሮ ዘመን ዠምሮ እስከ ዛሬ ድ ረስ ጐንደሬ ወይም ትግሬ ማለትና ከፉ ሰው ማ ለት ትርጉሙ አንድ ነው ለከፉ ሕዝብ በሚገባ ውም በባርነት አገዛዝ ሊገዙዋቸው ባልጠሉም ነበር። እቴጌ ጣይቱ ግን ለሰሜን ወገን ኹሉ ጋሻ ኹነ ው አገድዋቸው። እውነት ነው እስከ ዛሬ ድረስ ትልቅ የኾነ የቤተመንግሥት ሹመት ኹሉ ይልቁንም የምኒስትርነት ሥራ በሸዎች እጅ ብቻ ነው። የትግሬ የስሜን የበጌምድር የላስታ የጐጃም ልጅ የኾነም ኹሉ እንደውጭ ሰው እየተቈጠረ ከትልቅ የመንግሥት ምክር አይገባም። ትምርት ስለሌለው ግን የስሜን ሰው የዚህን ነገር ውርደት ገና አያስ ተውልም። በዚህ ምክንያት በሌላ ነገር ስላልተዋረደ ለጥ ብሎ ተገዛ።

የእቴጌ ጣይቱም አገልግሎት ይህ ብቻ አይዶለም ነገር ግን ስንቱን ብለን እንቈጠረው። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ በመሬት ላይ እስታለ ድረስ የጣይቱ ብጡል ስም አይረሳም። ስለዚህ የበኋላው ስሕተታቸው ያሳዝናል። የዳግማዊ ምኒልክን ፈቃድ ወራሻቸው የወሎው ባላባት የልጃቸው የወይዘሮ ሸዋረገድ ልጅ ኢያሱ ሚካኤል ይኹን የሚለውን አላስፈጽምም ብለው ተነሥተው ነበሩና። ስለዚህም ብዙዎች መኳንንት መዠመሪያ በጀርመኑ ዶክቶር ጽንትግራፍና ባስተርጓሚው በኋላ ግን በደጃች ገብረሥላሴና በነጋድራስ ኀይለጊዮርጊስ ተመክረው ተነሥባቸው ከቤተመንግሥት ጕዳይም እንዲከለከሉም የግድ አልዋቸው። የሚጠረጠሩ ዘመዶቻቸውም ኹሉ ታሰሩ። ይህም ኹሉ ሲኾን የወንድማቸው ልጅ ደጃች አመዴ ሲያዙ በቀር ደም አልፈሰሰም። ይህም አንድ ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው። ዐጤ ምኒልክ ሲደከሙ በኢትዮጵያ ብዙ ደም ይፈሳል ተብሎ በጠላቶቻችን ተስፋ ሲደረግ ኑሮዋልና። እውነትም የሸዋ መኳንንት መሰማማት በማጣታቸው የመንግሥታችን ጠላቶች ተስፋ ሊፈጸም ጥቂት ቀርቶ ነበረ። እግዚአብሔር ግን ዘወትር ቸርነቱ ዛሬም ብርቱ ጋሻ ኹኖ መንግሥታችንን ከጥፋት አዳነ።

## ፫

የኛ የኢትዮጵያዊያን ያለፈው ታሪክ እጅግ ያሳዝናል። ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ዠምሮ እስ ካኹን ድረስፍጹም የኾነ ሰላም አግኝተን አናውቅ ምና። የተወደደች አገራችን ዘወትር በጠላቶች ተከባ ስትኖር ነበረች ትኖራለችም። ነገር ግን በእግዚአብሔ ር ቸርነት የውጭ ጠላት ከዚህ በፊት አላዋረደን ም። አንድነትም ስንኾን ምንም የሚደፍረን እንደሌለ ስ ታሪክ ይመሰክራል። ዘወትርም በስምምና በፍቅር አድረን ብንኾን እስከዛሬ ድረስ ብዙውን ትልልቅ ነገር መፈጸም እንችል እንደነበር

ጥርጥር የለውም። እግዚአብሔር ብዙ በረከት ሰጥቶናልና። ትምርትን በ ቶሎ መቀበል የሚችል ልቦናና የጦረኛን ባሕሪ ማለፍያና ሀብታም አገርንም። ካለመስማማታችን የተ ነሣ ግን ሌሎች ሕዝቦች በአእምሮና በጥበብ እየበ ረቱ ሲኼዱ እኛ ወደኋላ ቀረን እንደአረመኖች እስኪቆጥሩን ድረስ። የዱሮውም ያኹኑም ኑሮዋችን እጅግ ያሳዝናል። በመላው ዓለም ላይ ሰላም ሲሰፋ አእምሮም ስትበራ እኛ በጨለማ እንኖራለን እርስ በርሳችን መጠራጠርንም አልተውንም ሕዝቦቹም ኹ ሉ እርስ በርሳቸው በፍቅር ተቃቅፈው ስለልማታቸ ው ባንድነት ኹነው ሲደክሙ እኛ አንድ ዘርና ወ ንድማማች መኾናችንን አልተገለጸልንም። እርስ በርሳች ን መፋጀትም እስከዛሬ ድረስ ጀግንነት ይመስለናል። ስለዚህም እግዚአብሔር ለብርታት የሚኾነውን ስጥ ወታ ሰጥቶን ሳለ ባለቤቶቹ ሰነፍነ። ሌሎቹም ነገሥታት እንደሰነፎች ይቆጥሩናል ይንቁናልም።

የሰውም ክብረቱ ሥራና አእምሮ መኾኑን ገና አላወቅንም። ስለዚህ መጽሐፍ የሚያውቀውን ወንድማችንን አስማተኛ ደብተራ የጅ ሥራ የሚያ ውቀውንም ቡዳ ፋቂም ሸማኔም እያልነ እናዋርደዋ ለን። መንግሥታችንም አንድ ጥበብ ከሚያውቀው ዜጋው ይልቅ ያነን የማያውቀውን ያከብራል። አኹ ን በቅርብም ጽሕፈት የማያውቀው መሀይምን ኹ ሉ ባዋጅ ሹመት ያልተከለከለ እንደኾነ መንግሥታ ችን ከቶ አይቀናም። ባገራችን እስከዛሬ ድረስ ሥር ተው ደከመው መብላት ነውር ነው። ለጭዋ ልጅም አይገባም ይባላል። ወታደር ተብሎ አሮጌ ጠመንጃን ም ተሸክመው አንድን ሹም እንደውሻ እየተከተሉ ከመዋልም በቀር ሌላ ክብረት አናውቅም። ያገራችን ም ሰው ኹሉ ወታደር ነኝ ባይ ነው። አንካሳውም ዕዉሩም ቆማጣውም በምርኩዝ የሚኼደው ሽማግሌ ውም አፍንጫውንም ያልጠረገ ልጅም ወታደር ነኝ ይላል። ሌላስ ይቅርና ብዙ ሰው በወታደር ስም ይ ጠራል ባደባባይም ሥራ ፈትቶ ሲክበሰበስ ይውላል መከረኛው ባላገር በደከመበትም እኽል ይመገባል። አእምሮ ባላቸው ነገሥታት ኹሉ ሥራት ወታደር ማለት በባላገሩና በገባሩ ላይ

ከፋት እንዳይመጣ የሚጠብቅ ማለት ነው። ባገራችን ግን የባላገር ደ መኛ ብለን ብንተረጒመው ልክ ነው። በዚህ ምክ ንያት ማለፍያዪቱ መሬታችን የሚያርሳት አጥታ ጠ ፍ ኹናለች ስለዚህም ደኸየነ። ባደባባይ ሥራ ፈት ተው ከሚኖሩቱ ሰዎች ግን ብዙዎች አርሰው ሊበ ሉ ባልጠሉም ነበር የሚወድቅባቸውን ዕዳ እየፈሩ ነው እንጂ። መሬትን ቆፍሮ ሊበላ የሚሻ ሰው ባ ገራችን መከራው ብዙ ነው። ገና ማረሻውን በመ ሬት ሳይተክል ግብር አምጣ የሚለው ሹም ይመ ጣል። ሲደክም ውሎም ወደቤቱ ሲመለስ ምሽቱን ወታደሮች ጋግሪ ወጥ ሥሪ እያሉ ሲያዳፍዋት ያ ገኛታል። ገዥዎቹም ባዘዙት ቊጥር የቤቱን ጒዳይ ጥሎ ቤታቸውን እንደባሪያ ደመወዝ አልባ ሲሠራ ይውላል። በያመቱም የሚከፍለውም ዕዳ አያውቅምና ሥጋት አይለየውም። አእምሮ ባላቸው ሕዝቦች ዘን ድ ግን እርሻን የሚዠምር ሰው እስኪደረጅ ድረስ ኹለት ወይም ሦስት ዓመት ምሉ በግብር አይነካ ም። ከዚህም በኋላ በያመቱ የሚከፍለው ግብር በ ሥራት የተለየ ነው ስለዚህም አይከብደውም። ወታ ደርና ሹምም ወደቤቱ ደጃፍ አይደርስም። ያ ለመ ንግሥቱ በያመቱ ሊከፍለው ከተደነገገውም ግብር በቀር ደክሞ የሚያገኘው ነገር ኹሉ ገንዘቡ እንደ ኾነ ያውቃልና ተግቶ ይሠራል። ተግቶም የሚሠራ ሰው ኹሉ ካልተቀማ በቀር ሀብታም ይኾናል። ሕዝ ቡም ሀብታም የኾነ መንግሥት ብርቱ ነው። ሕዝ ቡ የደኸየ እንደኾነ ግን ደካማ። እኛ ግን ሥርዐ ት የለንም ስለዚህም ሰነፍነ። በመሬታችን ውስጥ የተሸሸገውም ሀብት ፈላጊ አጣ ስለዚም ደኸየነ።

ጥጥን የሚያፈራና በግን ለማርባት የሚኾነ ው መሬታችን ሥራ ሲፈታ ከውጭ አገር የመጣ ውን የማይረባውን ጨርቅ እንለብሳለን። ከመሬታችን ም ውስጥ ብረትና ከሰል ሲገኝ መሣሪያችንን ኹ ሉ ከባሕር ማዶ እናስመጣለን። ሌላስ ይቅርና አን ድ ብልኀ የትግሬ ሰው እንዳለው መርፌንም ቢኾን ሠርተን አንችልም። የሀብታምም መሬት ጌቶች ሳለን እንራባለን። ይህም ድኽነትና ችጋር የስንፍናችን ፍሬ ነው።

በፊትኽ ወዝ እንጀራ ትበላለኽ ወደተፈጠር ኽባት ምድር እስክትመለስ ድረስ (ዘፍጥረት ፫፲፱) ፡፡ እግዚአብሔር ምድርን ፈጠረ፡፡ ለሠራተኛው ለብልኍ ሰውም በረከት ለሰነፉም አይዶል፡፡ ስለዚህም እነዚያ ሥራንና ትምርትን የሚወዱ ሕዝቦች ውለው አድረ ው በሰነፎቹ ሕዝቦች ላይ እንዲገተዩ የማይነቀነቅ ዘላለማዊ ሥርዐት ነው፡፡

ምነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከንቅልፍኽ መች ትነሣለኽ? በዓለም ላይ የሚደረገውን ነገር ለማየትስ ዐይንኽን መች ትከፍታለኽ?

ከላይ እንዳልነው እግዚአብሔር አምና መን ግሥታችንን አዳነልን፡፡ ስለኾነ ይገባናል እናውቅ ዘን ድ መንግሥት ያለው ሕዝብ ነው መባል ብቻ ጥቅምና ክብረት እንዳይኾን፡፡ እጀጠባብና ሱሪ አልባ ካባ ላንቃ ያልለበሰ ሰው መኰንን እንደማይኾን፡፡ ባለመንግሥት ከኾኑ ዘንድ እውነተኛ አእምሮ ያለ ው ባለመንግሥት መኾን ያስፈልጋል፡፡

በዙሪያችን ያሉትን አገሮች ብንመለከት አ እምሮ ያላቸው ሕዝቦች በብዙ ትጋት ሲያለምዋቸ ው እናያለን፡፡ ይልቁንም በደርቡሾች ጠፍቶ የነበረ ውን የሱዳንን መሬት ብናይ እንግሊዞችን የሚመስል የአእምሮ ሕዝብ ሲገዛው ምድረበዳም ቢኾን የደስታ ገነት እንዲኾን ይመሰክርልናል፡፡ በዙሪያችን ቅኞችን ኮሎንዮች ይዘው ያሉ ሕዝቦችም ያእምሮ ዋቸው ኀይል እንቅፋትን ኹሉ እያሸነፈ ወደፊት ይ ገፋል መሬት ጠቦታልና፡፡ አእምሮም በአእምሮ ካልኾነ በቀር በሌላ አትታገድም፡፡ ስለዚህ ወዮለት! በድን ቁርናው ለሚቀመጥ ሕዝብ ውሎ አድሮ ይደመሰሳ ልና፡፡ እኛ ኢትዮጵያዊያን ከፈረንጆች ጋራ ከተዋወ ቅነ ብዙ ጊዜ አልፈዋል፡፡ ነገር ግን እስከኹን ድረስ አንዳች አልተማርነም፡፡ ስለዚህም መንግሥታችን እንዳትጠፋ ያስሰጋል፡፡ የኢትዮጵያችን ሰው ግን ይህ ነን ቢነግሩት እንዲል ሲል ይመልሳል፡፡ እግዚአብሔ ር አገራችንን አሳልፎ ለባዕድ አይሰጣትም፡፡ የመንግ ሥታችንም መኳንንት ይህንን እያሉ በስንፍና ይኖራሉ እውነትም ቸሩ እግዚአብሔር የመንግሥታችን አርነት

እንዳትጠፋ ብዙ ጊዜ ከለከለ። እኛ ግን እ ስከዛሬ ድረስ ለቸርነቱ የተገባን ሕዝብ መኾናችንን አላሳየንም። በዚህ ምክንያት ውሎ አድሮ እንዳይፈር ድብን እንጠንቀቀቅ እንትጋም። መንግሥታችንም እ ንድትቀና የሚከተሉቱ ዐሥር ነገሮች በቶሎ ቢፈጸ ሙ ማለፊያ ነበር።

መዠመሪያ ለመንግሥት የሚኾን ገንዘብና ለንጉሡ የሚኾነው ገንዘብ በሥርዐት ይለይ። ሹሞ ችም ይደሩ። ካገር በሚወጣውም ምግብ ለመንግሥ ት ይግባ። የጦርም ሰራዊት ኹሉ የንጉሥ ይኹን። ያ ገር ምስለኔና የጦር አለቃ በያገሩ ይለይ። መዠመ ሪያው ባላገሮቹን የሚያዝ ኹለተኛው ግን ወታደሮቹን።

የንጉሡና የመንግሥት ገንዘብ የተባለውም ትርጉሙ እንዴህ ነው። የንጉሥ ገንዘብ ማለት ያ ለግብርና ለሌላ የንጉሡ ቤት ጉዳይ የሚያስፈልግ ገንዘብ ነው። የመንግሥት ገንዘብ ማለት ግን ያለሰራዊት ደሞዝ ለመንገዶችና ለትምርት ቤቶች ማስሠሪያ የጦር መሣሪያዎችም መግዣ ለሌላ እንዴህ የመሰለውም የውጭ ጉዳይ የሚኾነው ገንዘብ ነው።

ኹለተኛ ሕዝቡ ለመንግሥት የሚከፍለው ግብር እንደየሀብቱ መጠን ቍርጥ ኾኖ ይታወቅለ ት። የሕዝቡም ቍጥር በመዝገብ ይግባ። እንዴሁም በየዓመት የሚወለደውና የሚሞተውም የሚጋባውና የሚፋታውም በመዝገብ ይታወቅ።

ሦስተኛ ሕዝቡም የሚከፍለው ግብር በብ ር እንጂ በእኽል በፍሪዳም አይኹን። የመንግሥት ሥራ ኹሉም በባላገር አይሠራ በባለደመወዝ እን ጂ። ባላገሩም የሚከፍለው ግብር በመላው አገር ትክክል አይኹን ያውራጃው ሀብት እየታየ እንጂ። አኹን በጌምድር ስሜን ላስታ ጐጃም የጁ ወሎ ብዙ ብር አይገኝበትም ስለዚህ እንደሀብታዎቹ ሸዋና ትግሬ ሊገብሩ አይቻላቸውም።

አራተኛ ያማርኛ ቋንቋ ገና ሰዋስው አል ተበጀለትም። ስለዚህ መንግሥታችን ከያገሩ ሰዋስው የሚያውቁትን ሊቃውንት ሰብስቦ

ያማርኛን ቋንቋ ሰዋስው ቢያስወጣ ደግነው። በያገሩ አውራ ከተማ እንደኤሮጳ ሥርዐት ያበሻን ፊደልና ያማርኛን ቋን ቋ ማስተማሪያ ቤቶች ይከፈቱ። ባዲስአበባ በሐረር ጌ በጐንደር በአኵስም ግን አውራ የትምርት ቤቶ ች በንዲህ ያለ ሥርዐት ይቁሙ። በያንዳንዱ የትም ርት ቤት አራት የኤሮጳ መምህራንና ዐምስት ያበ ሻ መምህራን ይሹሙበት። የያንዳንዱ የኤሮጳ መም ህርም ሥራ ይህ ይኹን አንዱ የቁጥርና የሒሳብ አስተማሪ ኹለተኛው የዓለም ታሪክና ጆግራፊያ አ ስተማሪ ሦስተኛው የንግሊዝ ቋንቋ አስተማሪ አራተኛው የፈረንሳዊ ቋንቋ አስተማሪ። በአኵሱም ግን በእንግሊዝ ቋንቋ መምህር ፈንታ የኢጣልያ ቋንቋ አስተማሪ ቢሾም ይሻላል። ያበሾቹ መምህራን ሥራ ግን ይህ ይኹን አንዱ የወንጌል አስተማሪ ኹለተኛው ያማርኛን ቋንቋ አገባብ አስተማሪ ሦስተኛው የመንግሥታችንን ታሪክ አስተማሪ አራተኛው የፍት ሐነገሥት አስተማሪ።

ስላራቱም አውራ የትምርት ቤቶች የሚያስ ፈልጉን መምህራን ዐሥራስድስት የኤሮጳ ሰዎችና ኻያ አበሾች ናቸው። አንድ ደልዳላ የኤሮጳ መም ህርም በ፪ሺኽ ብር ላመት ይገኛል። ያበሻውም አን ድ አስተማሪ ፫መቶ ብር ባመት ቢያገኝ ይበቃዋ ል። ስለዚህ ለመምህራን የሚኾነው ደሞዝ በየዓመ ቱ ፻፳ሺህ ብር ነው። ለትምርት ቤቶችም ሌላ ጉ ዳይ ኹሉ ፻፹፪ሺህ ብር ይበቃል። ስለዚህ ላውራጃ ዎቹ የትምርት ቤቶች የሚያስፈልገው ኪሳራ ፻፶ሺህ ብር በየዓመት ብቻ ነው። ፊደልን ያላጠና ልጅም በአውሮቹ የትምርት ቤቶች አይግባ። የፊደል ማስተ ማሪያ ቤት ግን ያውራጆቹ ገዦች እንዲያስባቸው መንግሥት የግድ ይበላቸው።

ያገራችንም ሰው ፊደልን ለመማር ቢተጋ አገራችን ቶሎ በቀናች። ፊደልንም መማር እጅግ ቀላል ነገር ነው። በሱዳን መሬት የሚኖር አንድ ትጉህ የወሎ ልጅ ዕድሜው ፳፫ ዓመት እስኪኾን ድረስ ምንም አያውቅም ኑሮ አኹን ዐማርኛንና ዐረብኛን አጥርቶ ይጽፋል። ብዞችም ያገራችን ሰዎች የዚያን ብልኅ ዎሎዬ መንገድ ቢከተሉ አገራችን በተጠቀመች። ደግሞም የኤሮጳን ሠራተኞች አምጥተው ባዲስ አበባ በጐንደርም

እንዲሁም በአኵሱም የጅ ሥራ ማስተማሪያ ቤቶች ቢበጁ ማለፊያ ነበር። መንግሥትም ለንደዚህ ያሉ የትምርት ቤቶች ምንም ብዙ ዋጋ ቢያጠፋ ግድ የለም ነበር። ወድያ ው የሚያስፈልገውን ሥራ በነዚያ የትምርት ቤቶች ውስጥ ያሠራ ነበርና። እንደዚህ ያለ ጠቃሚ የትም ርት ቤት በካርቱም ከተማ ተበጅተዋልና መንግሥታ ችን ወደዚያ ተመልካች ይላክ።

ዐምስተኛ ፍትሐነገሥታችን ከዛሬው ያደባባ ይ ሥርዐት ጋራ አይሰማማም። ስለዚህ መንግሥት የሥርዐት ዐዋቆችን ሰብስቦ ከኤሮጳ ሥርዐት ጋራ የተስማማ ፍትሐነገሥት ያውጣ። ይህም ሲደረግ የ ኤሮጳ ሥርዐትን የሚያውቅ አማካሪ ያስፈልጋል። የ ተጻፈ ሥርዐት የሌለው መንግሥት ብዙ ዕድሜ የ ለውም።

ስድስተኛ ያገራችን ሰራዊት ሥርዐት የለው ም ስለዚህ የኤሮጳን መኳንንት አምጥተው ሰልፍን ቢማር ማለፊያ ነበር። እንዴሁም የኤሮጳን መምህራን አምጥተው ባዲስ አበባ ላይ የጦር ትምርት ቤት ይበጅ። ላገራችን የሚስማማ ማለፊያ ዐይነት የጦር ትምርት ቤትም በካርቱም ከተማ ተበጅትዋል። ስለዚህ መንግሥታችን ወደያ ተመልካች ይስደድ። የሰራዊት ም ብዛት በልክ ይኹን። ሰራዊት ቢበዛ መንግሥት ይደኸያል እንጂ አይበረታም።

ሰባተኛ የዛሬው የመንግሥታችን ብር የተበ ላሸ ነው። ሥርዐትና ውል የለውም። ባንዱም አወራ ጃ በጨው በሌላው በጥይት ይሸረፋል። ስለዚህ መንግሥት ለመላው ኢትዮጵያ የሚኾን የገንዘብ ሥርዐት በቶሎ ያላወጣ እንደኾነ ንግድ ሊለማ አ ይችልም።

ስምንተኛ ላገራችን ነጋዴ ሥርዐት እስኪወ ጣለት ድረስ መንግሥታችን አይቀናም። በሩና ቀራ ጩ ብዙ ነው። ከሦስት ዓመት በፊት አንድ ደፋር የጐንደር ነጋዴ በመተማ ግመሎች እንደተወደዱ ሰምቶ ግመሎችን ሊገዛ ወረደ። ገዝቶ ሲመላለስ ያገኘውንም እንዲህ ሲል አጫወተኝ ከጥልጣል መ ሬት ግመሎችን ይገዬ ተነሥቼ መተማ እስከገባ ድረስ ኻምስት በሮች

ላይ ቀረጥ ከፈልኹ። በየበሩ ም ጉቦ እስኪቀበሉ ድረስ በረኞቹ አናሳልፍም እያ ሉ መከራ ሲያበሉኝ ነበሩ። መተማም ደርሼ ግመ ሎችን ብሸጥ ስላገኘኹት መከራ የሚከስ ጥቅም አላፈራኹም። በዚህ ምክንያት ይህ ዐይነት ንግድ እነግዳለኹ ብዬ አይደግመኝም። ያሰው እውነቱ ነ ው። የግመሎቹም ንግድ ቢቀር የሚጐዳ እርሱ ብ ቻ አይዶለም ነገር ግን ከኹሉ ይልቅ ያገራችን መንግሥት ያገራችን ቀረጥ ሥርዐት ያለው ቢኾን ብዙ ግመሎች ሲሸጡ መንግሥት ገንዘብ ያገኝ ነበር። ነጋዶቹም በሚያገኙት ትርፍ በሬና ላም ገዝተው ወይም በሌላ ዐይነት ሥራ አገርን ባለሙ። ግመሎቹ አርጅተው እስኪሞቱ ድረስ የጥልጣልን ሜዳ ቢበሉ ግን መንግሥታችን የሚያገኘው ጥቅም ምንድር ነው።

ባንድ መንግሥት ውስጥ ብዙ በር ሊበጅ አይገባም። ለመንግሥት ትልቅ ጉዳት ነውና። ምነው ወደሱዳን ወይም ወደሐማሴን ተመልካቾች ሰደን ሥርዐት አንማርምን።

ዘጠነኛ ሕዝቡ ባንድ መንግሥት ውስጥ መኾኑን አጥብቆ እንዲታወቀው አገሩን የሚዞሩ ተ ቋጣጣሮች ይሹሙበት። እነሱም ባገር ግዛት ከሚኒ ስትር በታች ይኹኑ።

ዐሥረኛ የሃይማኖት አርነት ይታወጅ። የሃይ ማኖት አርነት ጥቅም መኾኑን የማያውቅ ብዙ ሰ ው ይኖራል። ስለዚህ የሚከተለውን ብናስተውል ደግ ነው። ያገራችን ሰው የተዋህዶ ሃይማኖት ከኹሉ ሃ ይማኖት ይበልጣል ብሎ ያምናል። በልጦ ግን ምን ረባን ማንስ ዐወቀው ያገራችን ካህናት መንግሥት ጠበቃቸው ኾኖ ሌላ ሃይማኖት ሊገባ እንዳይፈቅድ ዐውቀው ሃይማኖታቸውን ለሕዝቡ ሊገልጹለት አሳብ የላቸውም። ስለዚህ ሕዝቡ እንኳን ተዋህዶ ማለት ምንድር እንኾነ ሊለይ የክርስቲያን ሃይማኖትን አው ራ መሠረት የወንጌልን ቃል አያውቅም። ስለዚህ አጕል ቀረ የሃይማኖት አርነት እስኪታወጅ ድረስ ም አጓጕል ይቀራል። ለዚህም ነገር ምስክር በሐማ ሴን እናገኛለን። በዱሮ ዘመን

በዚያች አገር መሀ ይምንስ ይቅርና ብዙ ቄሶች ሃይማኖታቸውን ሳያው ቁ ይኖሩ ነበሩ። ጵሮተስታንቶችና ካቶሊኮች ከመጡ ወዲህ ግን ትልቁም ትንሹም ወንጌልን ቃል ዐው ቆ በትርጕሙ ይከራከራል። ካህናትም ባላምጣ ቢበዛ ባቸው ያስተምሩ ዠመር። በዚህ ምክንያት የሃይማኖ ት አርነት ቢታወጅ ሃይማኖት ታወቃል እንጂ አይጠፋም።

ደግሞም ባገራችን አንድ የድንቁርና ነገር አለ። ሃይማኖቱ ተዋህዶ ያልኾነ ሰው ኹሉ እንደርኩ ስ ይቆጠራል። ይህም እጅግ ያሥቃል። አእምሮ የሌ ለው ሕዝብ ኹሉ የእግዚአብሔርን ቃል ሳያውቅ የእግዚአብሔር ጠበቃ ሊኾን ይወዳል።

ሃይማኖት የልብ ነገር ነው ስለዚህ ሰማያ ዊው ንጉሥ እንጂ የዚህ ዓለም ንጉሥ አይቈጣጠ ረው። ወንጌል የቄሳርን ለቄሳር ስጡ የእግዚአብሔ ርንም ለእግዚአብሔር ያለውም በዚሁ ቢተረጐም ለ መንግሥታችን ሳይበጅ አይቀርም።

እንሆ ይህ ኹሉ ባጤ ምኒልክ ታስቦ ኑሮ ይኾናል ነገር ግን አልተፈጸምም። ስለዚህ በክቡር ወልዑል ወራሻቸው በልጅ እያሱ እንዲፈጸም ተስፋ እናድርግ። ክቡር ወልዑል የመንግሥት ወራሽም ይ ገባቸዋል ያውቁ ዘንድ ትልቅ ውርድ በራሴ በላያ ቸው እንደተሸከሙ። የዛሬው የኢትዮጵያ ንጉሥ ሥራ እንደዱሮዎቹ አይዶለም። የዚህ ዓለም ንግሥት በዱሮ ዘመን ድንቁርና ነበረች። ዛሬ ግን የማትቻ ል ብርቱ ጠላት ተነሣችባት እርስዋም የኤሮጳ አእምሮ ትባላለች። ለርስዋም ቤቱን የሚከፍት ክብረ ት ይጨምራል ቤቱን የሚዘጋባት ግን ይደመሰሳል። ኢትዮጵያችን የኤርጳን አእምሮ የተቀበለች እንደኾነ ግን የሚደፍራት ጠላት የለም። ያልተቀበለች እንደ ኾነ ግን ትፈርሳለች ወደባርነትም ትገባለች። በዚህ ምክንያት ክቡር ወልዑል ያጤ ምኒልክ ወራሽ የ ጃፓን መንግሥት እንዴት እንዳደረገ አስመርምረው መንገዱን እንዲከተሉት ተስፋ እናርግ። በጌምድሮች እንደሚሉት ባገራችን ርስት የተተከለ

በዳግማዊ ኢ ያሱ ነው። ስለዚህም በክብር ወልዑል ልጅ ኢያሱ ብርታት ደግሞ የኢትዮጵያው መሬት የኢትዮጵያዊያን ርስት እንዲኾን በብዙ እንመኛለን።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ በ1879 ዓ.ም. በአድዋ አካባቢ ተወለዱ፡፡ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ኤርትራ ውስጥ በሚገኘው የሲዊድን ሚሽን ከተማሩ በኋላ ወደ ጀርመንና አውስትራሊያ በመሄድ የሕክምና ትምህርታቸውን አጠናቀቁ፡፡ ከጀርመን ሚሽን ጋር ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በዓፄ ምኒልክ ቤተመንግሥት ፀሐፊ በመሆን ሠርተዋል። የምኒልክ ሐኪም ለነበረው ጀርመናዊ ዶክተር አስተርጓሚ ሆነው ሲያገለግሉ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በነበራቸው አለመግባባት አገር ለቀው ወደ ሱዳን ተሠደዱ፡፡ ከዛም ለሱዳን መንግሥት የሀገር ውስጥ ደኅንነት ሲሠሩ ቆይተው ወደሀገራቸው በመመለስ በቤተመንግሥት ውስጥ ማገልገል ጀመሩ፡፡ በመቀጠልም የድሬዳዋ ጉምሩክ ኃላፊ ሆነው ተመድበው በራስ ተፈሪና በሌሎች ተቀናቃኞች ወገኖች ተፈጥሮ በነበረው ግጭት ራስ ተፈሪን ወግነህል በሚል ከኃላነታቸው ተነሱ፡፡

እኚህ የኢኮኖሚ ፈላስፋና የሕክምና ምሁር በ1912 ዓ.ም. በኅዳር በሽታ ሕይወታቸው ቢያልፍም “መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር” በሚለው ዝነኛ መጽሐፋቸው የሀገሪቱን የውስጥ ጉዳይ አስተዳደርና ኢኮኖሚ እንዲሁም በትምህርት ላይ ፍጹም ለውጥ እንዲኖር አሳስበዋል፡፡ መጽሐፋቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው በአቶ ጳውሎስ ኞኞ አማካይነት ነው፡፡

## የደራሲው ሥራዎች

1. ዐፄ ምኒልክና ኢትዮጵያ(ታሪክ)
2. መንግስትና የህዝብ አስተዳደር

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY